March 31, 2010

# Symposium on Ethiopian Current Issues March 27 2010፡Report

Sponsored by the Ethiopian Unity Diaspora Forum (EUDF), the United Ethiopian Democratic Forces (UEDF), and the Ethiopian People's Revolutionary Party — D)

## የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ጉባኤ በዋሺንግቶን ዲሲ ሚያዝያ 18 2002 የሲምፖዝዮሙ ዘገባ

በሚያዝያ 18 በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ዋሺንግቶን ዲሲ የተካሄደውን ጉባኤ ስኬታማና አመርቂ ከመኖሩም በላይ አነስ ባለ መልኩ ገንቢ የሓሳብ ልውውጦች ስለተካሄዱና ለወደፊቱ ዓብይ ጉባኤ መንደርደርያ ይሆናል ብሎ ስለታመነ በጉባኤው መሳተፍ ላልቻሉት ኢትዮጵያውያን ትምህርት ይሆን ዘንድ በዘገባ መልክ አቅርበነዋል።

በጉባኤው የተሳተፉ ግለሰቦች፡ ስብስቦች፡ የፓርቲና ሲቪክ ማህበራት ተወካዮች ለኢትዮጵያ ሃገራቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ተቆርቋሪነት በከፍተኛ ደረጃ ከገለጹ በኋላ በሲምፖዝዮሙ ፕሮግራም መሰረት የቀረቡትን ዓበይት ነጥቦችን አንድ በአንድ፡ በግልጽና በስፋት እንዲሁም ገንቢ በሆነ መንፈስ የሚከተሉትን የውይይት ርእሰ-ነገሮች ተወያዩባቸው፦

1. የኢትዮጵያ የ2002 ምርጫ
2. የኢትዮጵያ ልዓላዊነት፡ አንድነትና ነጻነት
3. ለውጭ ሃብታሞችና ሃገሮች የተሸነሸኑት የእርሻ መሬቶች
4. የኢትዮጵያ ሃገራዊ ድኅንነት

ከነዚህ አራቱ ርእሰ ነገሮች ግን ቤቱ በይበልጥ ያተኮረው በ2002 ምርጫና በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ነጻነት ላይ ነበር። ምርጫውን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች ተሰንዝረዋል፦ 1) ካለው ጸረ-ዴሞክራሲና አምባ ገነናዊ ስርዓት በማዛመድ የምርጫ ሂደት ከተገነዘብነው ገና ለገና ሕዝቡ በሚፈልገው መንገድ ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው። በግልጽ እንዳየነው ያለው መንግስት በልዩ ልዩ ቦታዎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት፡ በተለይም ለውድድር እጩ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፡ እያበሳጨ፡ እያሰረና እየገደለ ነው ያለው። የአረጋዊ ገብረዮሃንስ በትግራይ አረሜናዊ በሆነ መንገድ መገደል የዚሁ የመንግስት እኩይ ተግባር ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ተመሳሳይ ድርጊቶችም በመሃልና ደቡብ ኢትዮጵያ ተካሂደዋል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ሆን ብሎ ልዩ ልዩ ሰበብና ምክንያት በመፍጠርና ተጽእኖም በማድረግ የኢህአዴግ አባላት በሦስት እጥፍ እንዲያድጉ ከማድረጉም በላይ ለእነኚህ አዲስ አባላት አዳዲስ መመዘኛዎችና ቅድመ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለኢህአዴግ እንዲመርጡ በማስገደድ ላይ ይገኛል። ከዚህ

አልፎ ተርፎ በገጠር አከባቢ ለአራሾች ማዳበርያ እንደ ግቦ በመስጠት ኢህአዴግ የሚመረጥበት ሁኔታ እያስተካከለ እንደሚገኝ ታውቋል። ስለዚህ ከዚህ ተጫባጭ እውነታ አንጻር ስናየው ምርጫ 2002 አስመልክቶ ብሩህ ተስፋ የሚያሳይ አይመስልም። በሰተጨማሪም ኢህአዴግ ምርጫውን ለመቆጣጠር በሚል ፊሊጥ አባላቱና አዳዲሶቹ ምልምሎች የስድስት ወር የመታወቅያ ወረቀት እንዲኖራቸው ደንግጓል፣ ምርጫውን በይበልጥ ለመቆጣጠር ደግሞ አምባገነኑ መንግስት የውጭ የብዙሃን የዜና ማሰራጫዎች እንደ አመሪካን ድምፅ እና ዶቸቨለ የአማርኛ ፕሮግራሞች በማጨቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ መረጃ እንዳያገኝ እያደረገ ነው። 2) ከላይ የተጠቀሰውን የቤቱ አመለካከት እንዳለ ሆኖ ምርጫውን አስመልክቶ በሩህ ተስፋ የታያቸው የቤቱ አባላት ደግሞ ነበሩ። ይኸም ከስሜት የመነጨ ሳይሆን ካለው ተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታና የተቃዋሚ ኃይሎች በያዙት የትግል ስልትና በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ የተመረኮዘም ነው። ከዚህ አኳያ መድረክ ደህና አቅጣጫ እንደያዘና በልዩ ልዩ ክልሎች ኢህአዴግን በማስበርገጉ፣ ልዩ ልዩ የሕዝብ ስብሰባ ጠርቶ ከሕዝቡም ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘቱ። በአንዳንድ አከባቢ እንደ ትግራይ፡ አዲስ አበባና ኦሮምያ ደግሞ ሕዝቡ ኢህአዴግን በመቃወም ለመድረክ እንመርጣለን ማለቱ፣ በተለይም በትግራይ ጥሩ ሁኔታዎች መፈጠራቸውና ለመለስ መንግስት አርእድ-አንቀጥቅጥ ለመሆኑ በምርጫ 2002 የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድል እንደሚቀዳጁ ቤቱ አይቶታል። ይኸንን አመለካከት በቤቱ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝም፡ አጠቃላይ የቤቱ ስሜትና ራእይ ግን ምርጫው ብዙ ውጣ ውረድ እንደሚኖሮውና መስዋእትነትም እንደሚከፈልበት መገንዘቡን ከተስማማ በኋላ ባሁኑ ምርጫ መድረክ ባያቸንፍና የመንግስት ሥልጣን ባይጨብጥም ቅሉ በፓርላማ ውስጥ ግን በርካታ ወንበሮች ይዞ ጠንካራ ተቃዋሚና የሕዝብ ጠበቃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል።

በቤቱ የተሳተፉ ግለሰቦች እጅግ ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ለአገራችንና ለሕዝባችን ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ገንቢ ሓሳቦች ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት አስቀምጠነዋል፦

1. በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ረገጣ አስመልክቶ የብርቱኳን መደቅሳ መታሰርና የአረጋዊ ገበረዮሃንስ መገደል በሰፊው ከተመለከተ በኋላ በተለይ የብርቱኳን የጤና ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ሆኖ ባስቸኳይና ያላንዳች ቅድመ-ሁኔታ እንድትፈታ ውሳኔ አሳልፏል። ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ፡ ሀ) ጽሑፎችና መግለጫዎች በየድረገጾች መለጠፍ፣ ለ) የአመሪካ ኮንግረስ አባላትን በጽሑፍና በስልክ በመደወል በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ተጽዕኖ እንድያደርጉ ማድረግ።
2. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አንድ ላይ የሚመጡበት ሁኔታዎችን መፍጠርና በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ባገራችን የመንግስትና የስርዓት ለውጥ ይኖር ዘንድ ተቃዋሚ ኃይሎችን - በተለይ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት ለሚታገሉ ፓርቲዎች - ድጋፍ መስጠት።
3. ተቃዋሚ ኃይሎች እርስ በራሳቸው እንዲቀራረቡ፣ የጋራ አጀንዳዎችና የትግል ስልቶች ለመቀየስና ለማዳበር ከፈለጉ መጀመርያ መደረግ ያለበት የመቻቻል ባህልን ማጐልመስ ነው። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ተቻችለውና ተከባብረው ሲታገሉ ብቻ ነው ድል ሊቀዳጁ የሚችሉ፣

የመንግሥት ስልጣን መጨበጥ የሚችሉም በቅድምያ የተስተካከለና የረጋ የሽግግር ወቅት ሲፈጥሩ ብቻ ነው። ይኸንን አስመልክቶ ቤቱ አገር ቤት የተፈጠረውን የተቃዋሚ ኃይሎች ባንድነት መስራት ተስፋ የሚሰጥ መሁኑን ቢገነዘብም፣ በውጭ የሚገኝ ተቃዋሚ ኃይል ግን በተናጠል በመስራትና በመነጣጠል ለጋራ የፖለቲካ ክንውኖች ዕንቅፋት መሆኑን ተገንዝቦታል። ይኸንን ችግር አስመልክቶ ቤቱ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ምሁራን መፍትሔዎች ለማቅረብ ልዩ ሚና መጫወት እንዳለባቸውና የፓርቲ አመራሮች ደግሞ 'ራሳቸውን በመግዛት' ለሌሎች አባላት አርአያ መሆን እንዳለባቸው አሳስቧል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉን ነገር ለምሁራንና ለፓርቲ አመራሮች ብቻ መተው እንደማይቻል የጋራ ስምምነት ተደርሷል።

4. ለዚሁ ለተቃዋሚ ኃይል በኢትዮጵያ-አቀፍ በመደራጀትና በመንቀሳቀስ አስፈላጊነት ቤቱ ትኩረት የሰጠበት ምክንያት፣ ሀ) በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በፈጠረው የጎሳ ፖለቲካና ለ) አንዳንድ ኢትዮጵያውያን - በተለይም በውጭ የሚገኙ - በጎሳ ዙርያ መደራጀታቸው ኢቀጥታዊ በሆነ መንገድ የኢህአዴግን ዘመነ-መንግስት ስላራዘሙ ቤቱ በዚሁ ረገድ ሰፊ ትምህርታዊ ዘመቻዎች መካሄድ እንዳለባቸውና መላ ኢትዮጵያን ያስተናገዱ (በይዘትም በመልክም) ድርጅቶች በቅድምያ ድጋፍ እንድያገኙ ቤቱ ተስማምቷል። ተቃዋሚ ኃይሉ ከጎሳ ፖለቲካ ባሻገር ካልተንቀሳቀሰ ግን ያለው መንግስት አገሪቷን አፈራርሶ ሊሄድ እንደሚችል አሳስቧል። ኢትዮጵያ አገራችን የብዙ ሺ ዘመን ታሪክ ያላትና ነጻነቷን ጠብቃ የቆየች ለመሆኗና ሕዝቧም በቀላሉ እንደማይበገር በቤቱ ዘንድ ስምምነት ቢደረስም ጥንቃቄ ካልተደረገ ግን የመፈረካከስና የመበታተን ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ቤቱ ተገንዝቦታል። በአንጻሩ አንዳንድ የቤቱ አባላት የዘር ፖለቲካ ጉዳይ እየተሰበረ መምጣቱና መስመር ካስያዝነውና ጉደለቶቹን አሻሽለን መቀጠል ከቻልን አወንታዊና ውጤታማ ሁኔታ እንፈጥራለን ያሉም ነበሩ።

5. ከጎሳ ፖለቲካ ባሻገር ለመስራት ከተፈለገም ብያንስ ብያንስ የሚከተሉትን በግብር መተርጎም እንዳለባቸው ቤቱ ተስማምቷል፦ ሀ) ሊያሰባስቡ የሚችሉ አጀንዳዎች ማቅረብ፡ ለ) የሚያቀራርቡ የትግል ስልቶችን መቀየስ፡ ሐ) የፓርቲ አመራሮች ራሳቸውን የችግር አካልና መፍትሔ መሆን፡ መ) የጎሳ ፖለቲካ ቅስቀሳ ለሚያካሄዱ የመንግስት ካድሬዎች በንቃት መከታተልና በነሱ ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ማድረግ፡ ሠ) በምርጫ 2002 ለሚሳተፉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ግለሰቦች ድጋፍ መስጠት፡ ረ) ምርጫ 2002 ነጻና ፍትሓዊ ይሆን ዘንድ ሰፊ ዘመቻ ማካሄድ።

6. በፖለቲካ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሴቶች በይበልጥ የሚሳተፉበትና የሚደራጁበት መንገዶችን መፍጠር።

7. የኢትዮጵያ ወጣቶች በሰፊው ፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፉበት መንገድ መጥረግ፣ በኢትዮጵያ የአሁኑ ተቃዋሚ ኃይሎች የአመራሮችን ችቦ ተረክበው የሚመሩበት መንገድ መቀየስ። በተለይም በ25 በ30 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች (ሴትም ወንድም) የነገ የኢትዮጵያ መሪዎች መሆናቸውን መገንዘብ። በውጭ አገር ለተወለዱት ወጣት ኢትዮጵያውያን ባህላቸውና ታሪካቸውን የሚያውቁበት የትምህርት መድረኮችን መፍጠር።

በማጠቃለልም ቤቱ መጀመርያ ጉባኤውን በመተባበር ለጠሩት ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ አንድነት ዳያስፖራ መድረክ (EUDF)፡ ኅብረት (UEDF) ና ኢ.ህአፓ-ዴን የጥልቅ ምስጋና ካቀረበላቸው በኋላ የቀረቡት ተጨማሪ አስተያየቶች ቢኖሩ፦ ሀ) ምሁራኑ በይበልጥ ጥናታዊ ጽሑፎችን ማቅረብ፣ ከተቻለም የጹሓፊዎች ሊግ መመስረት፡ ለ) ምሁራኑ በእንግሊዝኛ ብቻ ሳይሆን ሕዝባችን በይበልጥ ይማር ዘንድ በአማርኛ (ከታቻለም በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች) መጻፍ እንዳለባቸው፡ ሐ) የጉባኤው ጽንሰ-ሓሳብ ጅምር የEUDF ስለሆነ ድርጅቱ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብቻ ጋብዞ ሌሎቹን ማግለል ስሌለበት ለወደፊቱ ብቻውን ገለልተኛ በመሆን ሁሉንም ፓርቲዎች ማስተናገድ ይኖርበታል።

ጉባኤው በታላቅ አወንታዊ መንፈስ ተገባዷል፣ ለወደፊትም ሰፋ ባለ መልኩ ሌላ ሲምፖዝየም እንዲጠራ የጋራ ስምምነት ተደርሷል።